የሰበር መ/ቁ. 23881

2/10/98

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፦ አቶ አብደላ ተጂ አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ክሱን ለመስማት ሲሆን ተጠሪ አልቀረበም፡፡ አመልካች በ2/10/98 በተፃፈ የቃለ መሐላ ማመልከቻ ተጠሪ መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፆ መጥሪያውን መልሷል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

ተጠሪ ክስ በሚሠማበት ቀን ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ይታያል፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች ነ/ፈጅ ሲያስረዱ ተበዳሪ/ከፋይ ሲመጣ መጀመሪያ የሚከፈለውን ገንዘብ ልክ ይሞላና ለተቀባዩ ይሠጣል ተቀባዩ ገንዘቡን ያረጋግጣል፡፡ የተቀበለውን ገንዘብ በኖት በኖት ለያይቶ ይፅፋል ማለትም ባለመቶ ኖት፣ ባለሃምሣ ኖት ወዘተ ብዛቱን ለይቶ ይፅፋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ደረሰኙ ላይ ያለውን የገንዘብ መጠን የሞሉት ተጠሪ ናቸው፡፡ በዛ ላይ ተጠሪው ቀሪ ዕዳ አለባቸው፡፡ ቀሪ ሂሣብ የለባቸውም በማለት ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የገለፀው በራሱ ነው ብለዋል፡፡

ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን የውሣኔ አግባብ ካለው የሕጉ ድንጋጌ አኳያ መርምሯል፡፡

11-11-98

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሣኔ የሠጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ባንክ ለተበደሩት ብድር ከከፈሉት ገንዘብ ውስጥ ብር 6000 የከፈሉበት ደረሠኝ ላይ በቁጥር 600 ብር በአሃዝ 6000 ብር ተብሎ በመፃፉ ባንኩ 600 ብር ብቻ እንደከፈሉ በመቁጠር ቤታቸውን በሃራጅ ሊሸጠው ስለሆነ ሽያጩ እንዲታገድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠሪ የከፈሉት ገንዘብ ብር 6000 ቢሆንም ቀሪ እዳ ስላለባቸው ባንኩ ቤታቸውን እንዳይሸጥ ሊያግድ የማይችል መሆኑን ገልፆ በዚህ በኩል የቀረበውን የተጠሪውን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ተጠሪ የከፈሉት ብር 6000 ከመሆኑም ሌላ ቀሪ እዳ የሌለባቸው በመሆኑ ቤታቸው ሊሸጥ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም በባንክ ሥራ የሂሣብ አሠራር ስህተት ሲፈፀም ውጤቱ ምንድነው የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አዞ ተጠሪም ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ለአመልካች ለከፈሉት ገንዘብ የተሰጣቸው ደረሠኝ ላይ በአሃዝና በቁጥር የተገለፀው የገንዘብ መጠን ልዩነት ያለው ቢሆንም ሁለቱም ፍ/ቤቶች 6000 ብር ተብሎ በአሃዝ የተፃፈውን ደረሰኝ ባንኩ ራሱ ያዘጋጀው በመሆኑ ሰነዱም በሰው ማስረጃ ሊስተባበል ስለማይችል ተጠሪ የከፈሉት ይህንኑ ገንዘብ ነው ሲሉ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተጨማሪ ይኸው የገንዘብ መጠን ደግሞ ሲቀነስ ተጠሪ ቀሪ እዳ አይኖርባቸውም በማለት ቤታቸው እንዳይሸጥ ወስኗል፡፡

በዘወትር የሂሣብ አሠራር በአንዳንድ አጋጣሚዎች የሂሣብ ስሌት ወይም የቁጥር አፃፃፍ ስህተት ሊፈጠር የሚችል መሆኑ አሌ የሚባል አይደለም፡፡ ይህ አይነቱ ስህተት በሚፈጠርበት ጊዜ ግን ስህተቱ ሊታወቅ የሚችለው አስፈላጊው ማስረጃ ሁሉ ቀርቦ ሂሣቡ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 11-11-98

ተጣርቶ ከቀረበ በኋላ ነው፡፡ ማንኛውም ፍሬ ነገር ሕጉ በሌላ አኳኋን እንዲረጋገጥ ወይም እንዲስተባበል ገደብ ካላበጀለትም በቀር በየትኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊረጋገጥ ወይም ሊስተባበል የሚችል በመሆኑ የሂሣብ ስህተት መፈጠሩን ማስረዳት የሚችል በቂ ማስረጃ ሁሉ ሊቀረብ ይችላል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ ለተጠሪ የተሠጠው ደረሰኝ ላይ በቁጥርና በአሃዝ በተገለፀው የገንዘብ ልክ በአፃፃፍ ስህተት ምክንያት ልዩነት በመፈጠሩ ተጠሪ የከፈሉትን ትክክለኛ የገንዘብ መጠን ማወቁን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት በደረሰኙ ላይ ከተገለፁት ሁለት የተለያዩ የገንዘብ መጠኖች ውስጥ በትክክል የተከፈለውን ገንዘብ ለማወቅ ይቻል ዘንድ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሁሉ ቀርቦ ሊታይ ይገባል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ደረሰኙ በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል እንደማይችል አድርገው በአመልካች የውስጥ ተቆጣጣሪ አዲተሮች ተጠሪው ብር 600 (ስድስት መቶ) ብቻ የከፈሉ መሆኑ ተረጋግጦ የቀረበውን ያለበቂ ምክንያት ሳይቀበሉት ቀርተዋል፡፡ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ማስረጃ መቀበልም ሆነ ውድቅ ማድረግ ያለባቸው ሕጋዊ ምክንያት ሲኖራቸው ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች በአሃዝ የተፃፈው በቁጥር ከተፃፈው የበለጠ ተቀባይነት ያገኘበትን ሕጋዊ ምክንያት ካለመግለፃቸውም ሌላ በአዲተሮች ተረጋግጦ የቀረበውን ማስረጃ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የከፈሉት ብር 6000 (ስድስት ሺህ) ነው ሲሉ የደረሱበት መደምደሚያ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25807 በ18/04/98 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04442 በ26/07/97 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

3/ ተጠሪ የከፈሉት ብር 600 (ስድስት መቶ) በመሆኑና ቀሪ ዕዳ ያለባቸው በመሆኑ ባንኩ ቤታቸውን በጨረታ እንዳይሸጥ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 11-11-98

የለውም:: በመሆኑም ጨረታው ሊቀጥል ይገባል::

4/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ:: መዝገቡ ተዘግቷል::

ለመ/ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

ተ.ወ ፊርማ [illegible] ቀን 11-11-98